# ተጠየቅ ሙግት
# ልማዳዊው የኢትዮጵያ የክርክር ሥልት

አበራ ጀምበሬ*

የተጠየቅ ሙግት ባለፈውና በያዝነው ክፍለ ዘመን በመጀመሪያዎቹ ሦስት አሥርተ ዓመታት ውስጥ ከፍ ካለ ደረጃ የደረሰ፥ ፍጹም ኢትዮጵያዊ የሆነ ልማዳዊ የፍርድ ቤት የክርክር ሥልት ሲሆን፥ ይኸውም የሕግ ዓይነት በዘመናዊ የሕግ ሳይንስ የፍትሐ ብሔርና የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ በመባል ይታወቃል። ይህም ሥርዓት በቃል ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲወራረስ የመጣ ነው።

ይህ የሥነ ሥርዓት ሕግ በተራቀቀ የጥያቄና መልስ /በክሮስ ኤግዛሚኔሽን/ ሥልት የነገርን ጭብጥ አፍረጥርጦ ለማውጣት የሚደረግ ሙግትንና የማስረጃ አቀራረብን /ሩል ኦፍ ኤቪደንስ/ ያጠቃልላል። "ተጠየቅ" የሚለው ቃል በቀጥታ ትርጉሙ "ልጠይቅህ" ማለት ሲሆን፤ በቴክኒካል /በሕጋዊ/ ትርጉሙ ግን ልማዳዊ የኢትዮጵያ የክርክር ሥልት ማለት ነው። "እሰጥ አገባ"[1] የሚለው ቃል በዚህ ዓይነቱ የሙግት ሥልት፥ በፍርድ ቤት የሚደረግ ክርክር ሂደትን የሚያመለክት በመሆኑ ለተጠየቅ ሙግት በተለዋጭ ቃልነት ያገለግል ነበር። ሙግት ማለት በፍትሕ አስተዳደር ክርክር ማለት ሲሆን፤ ሥነ ሥርዓት ነክ የሆኑ ጉዳዮችን ሁሉ ያጠቃልላል።

ጀኔራል ሸርጃን በዚህ ፍጹም ኢትዮጵያዊ በሆነው የሙግት ሥልት መሠረት ሲካሄድ ስለተመለከቱት የፍርድ ቤት ክርክር የሰጡትን ሐተታ ሲያጠቃልሉ፤ የዓይን ምስክርነታቸውን በሚከተለው አኳኋን ገልጸውታል።

---

* በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሕግ ፋኩልቲ የትርፍ ጊዜ ረዳት ፕሮፌሰር

ኢትዮጵያዊ ጥሩ ተናጋሪ ስለሆነ፥ ተሰጥኦውን ለመግለጽ የሚችልበትን ማንኛውንም ዕድል ሳይጠቀምበት አያልፍም። ሙግት ብዙውን ጊዜ ብዛት ያለውና አድናቂ አዳማጭ የሚሰበሰብበት ጥሩ አጋጣሚ ነው። አንዳንድ ጊዜ ትክሻውን እያሳየ፥ አንዳንዴም ጣቱን ወደ ተከሳሹ እየቀሰረ በሚያስፈራራ አኳኋን ሲቃ እየተናነቀው የነገር ፍላፃውን ያንበለብለዋል።

ዳኛውም ዙሪያውን በከበቡት አድማጮች መካከል ተቀምጦ እንደበተ ርቱውን ተከራካሪ በጥሞናና በተመስጦ ከአዳመጠ በኋላ ተከሳሹን መልስ እንዲሰጥ ይጠይቀዋል። እርሱም ከምንጭ ገንፍሎ እንደወጣ ፈሳሽ ተፍ ብሎ ይነሳና ንጹህነቱን እንዲመሰክርለት እጆቹን ወደ ሰማይ እንደዘረጋ በርከክ ይላል። በተከራካሪውም አፍንጫ ሥር ቡጢውን ያወዛውዛል። ከመሳሉ የቃላት ውርወራውን ሳያቋርጥ፥ እጆቹን አጣጥፎ ወደዳኛው ይቀርባል።[2]

ይህ የፍርድ ቤት ቲያትራዊ ገለጻ የአማራ ባሕላዊ ቅርስ /ውርስ/ አካል የሆነው የተጠየቅ ሙግት እንዴት ይካሄድ እንደነበር ያሳያል። ከ1928 ዓ.ም. በፊት የአማራ ልማዳዊ ሕግ፥ ከተጠየቅ የሙግት ሥርዓት ጋር በአብዛኛው የኢትዮጵያ ክፍል ጎልቶ ይታይ ነበር።

እዚህ ላይ መነሳት የሚገባቸው ጥያቄዎች፥ በተጠየቅ ሙግት አፈጻጸም አግባብነት የነበራቸው ዋና ዋና ሁኔታዎች ምን ነበሩ? እንዴትስ ይሠሩ ነበር? የሚሉት ናቸው።

## 1. <u>በፍርድ ቤት የሚካሄዱ ሁኔታዎች</u>

ሙግት ሲጀመር አብዛኛውን ጊዜ በበጎ ፈቃድና ከመቅጽበት የሚፈጸም የግልግል ሂደት ሁኖ ነበር። አንደኛው ወገን ተከራካሪ ባላጋራውን መንገድ ላይ ሲያገኘው ማንኛውም ተላላፊ መንገደኛ ጉዳዩን በዳኝነት እንዲያይለት /እንዲዳኘው/ የመጠየቅ መብት በሕግ ተሰጥቶታል።[3] ክርክሩ የሚያገባው ወገን የተላላፊ መንገደኛው

/የመንገድ ዳኛ ፍርድ ቤት/[4] ውሳኔ ቢያረካው ጉዳዩ በዚሁ እንዳለቀ ይቆጠራል። ለሁለቱም ተከራካሪ ወገኖች ወይም ለአንደኛው እርኪ የሆነ ውሳኔ ያልተገኘ እንደሆነ ግን ወደ ፍርድ ቤት ተያይዘው ይሄዳሉ፤ ወይም አንዳንድ ጊዜ የመንገድ ዳር ዳኛ ሁኖ የዳኛቸው ሰው በአቅራቢያ ከሚገኘው ዝቅተኛው የመደበኛ ፍርድ ቤት ዳኛ ዘንድ ያደርሳቸዋል።

ዝቅተኛው የመደበኛ ፍርድ ቤት ዳኛ ጭቃሹም[5] ወይም መልከኛ[6] ሊሆን ይችላል። ጭቃሹምና መልከኛ በመሠረቱ የዳኝነት ሥልጣን ያላቸው የአስተዳደር ሹማምንት ነበሩ። በዚያ ጊዜ ለነበረው ሕብረተሰብ የመንግሥታዊ ሥልጣን መከፋፈል መሠረተ ሃሳብ እንግዳ ነበር። ስለዚህ የመንግሥት ባለሥልጣን ሁሉ ዳኛ ይባል ነበር።

በዳኝነት ሥራ አግባብ ካላቸው ከዳኞች ቀጥሎ ከፍተኛ ሥፍራ የነበራቸው ተቺዎች /አማኞች/[7] ነበሩ። ከአማኞቹ ከፊሎቹ በተከራካሪ ወገኖች ከፊሎቹ ደግሞ በፍርድ ቤቱ ከተገኙ ሰዎች መካከል በመደበኛው ፍርድ ላይ የሚመረጡ ነበሩ።

በፍትሕ ሥራ ዓይነተኛ ሂደት ውስጥ ሦስተኛ ደረጃ የሚሰጠው ደግሞ ዋስ ነበር። ብዙውን ጊዜ የሚዘወተሩት የዋስ ዓይነቶች የሚከተሉት ናቸው።

1. የቅብታብ ወይም የመጋኛ ዋስ:- አንድ ወንድ ለአካለ መጠን ደርሶ የራሱ መኖሪያ ቤት ሠርቶ ጎጆ ሲወጣ፥ የኅብረተሰቡ ሥርዓት ተሩ አክባሪ እንደሚሆን ለማረጋገጥ የሚጠራው ዋስ፤

2. የሥነ ሥርዓት ዋስ:- ክስ ሲጀመር በሙግት ወቅት የሥነ ሥርዓት ሕግ የሚጠይቀውን ሁሉ ለማክበርና ለማሟላት፤ እንደዚሁም ነገሩ በሚሰማበት ቀን ቀጠሮ እንደሚቀርቡ ለማረጋገጥ ሁለቱም ወገኖች /ከሳሽና ተከሳሽ/ የሚጠሩት ዋስ፤

3. የነፈ ዋስ:- ከተከራካሪ ወገኖች አንደኛው በሌላው ላይ ወንጀል አውርቶ ወይም ተሳድቦ እንዳይቀር፣ በተናገረው ካልነፋበት ስለሚቀጣ፤ ለካሣው ክፍያ የሚጠራው ዋስ፤

4. የዳኝነት ዋስ:- በሙግት የተረታው ወገን ለመንግሥት ዳኝነት መክፈል ስለሚኖርበት፤ የዳኝነቱን ለመክፈል በሁለቱም ወገን የሚጠራ ዋስ፤

5. የውርርድ ዋስ:- በክርክሩ ወቅት ይህን እሰጥ ብሎ የሚተክለውን ውርርድ ተረቺው መክፈል ስለአለበት፣ አከራካሪ ሆኖ የተገኘው ጉዳይ ብይን ሲሰጥበት፣ የውርርዱን ለመክፈል የሚጠራ ዋስ፣

6. የበሰላ ዋስ:- በፍትሐ ብሄር ጉዳይ ክስ የተረበበትን ዕዳ ለመክፈል ፍርድ በሚሰጥበት ወቅት የሚጠራ ዋስ፤

7. የጠለፋ ዋስ:- አንድን ሰው እጁን ለማቅረብ ወይም ዕዳውን ለመክፈል ዋስ የሆነው ሰው በፋንታው ተጠያቂ የሚሆንለት ሰው እንዲሰጠው ጠይቆ የሚያስጠራው ዋስ፤

8. የእጅ ጠብቅ ዋስ:- በወንጀል ክርክር በማንኛውም ደረጃ ለሕይወቱ ያስጋኛል ብሎ አንደኛው ወገን ሲያመለክት የእጅ እላፊ እንዳይፈጽም ሌላው ወገን የሚጠራው ዋስ።[8]

በዚህ የሙግት ሥርዓት በፍትሕ ሂደት አራተኛውና የመጨረሻው ነገረ ፈጅ የሚባለው ተቋም ነው። ነገረ ፈጅ የሚሆን ሰው በአብዛኛው በቂ የሕግ እውቀት ያለው ሆኖ፣ አንድን ሰው በመወከል በፍርድ ቤት ለመቆም የተስማማ ሰው ነው።

በፍትሕ ሂደት አግባብ ያላቸውን ተቅዋማት ከገለጽን ዘንድ፥ የተጠየቅ ሙግት እንዴት እንደሚካሄድ፤ ማለትም በማንኛውም ደረጃ በሚገኝ መደበኛ ፍርድ ቤት የሙግቱ ሂደት እንዴት እንደሆነ ወደ መግለጽ እናመራለን።

## 2. የፍርድ ሂደት

### ሀ/ ክርክር መጀመር

በከሳሹና በተከሳሹ በሁለቱም የሥርዓት ዋስ በመጥራት በፍርድ ቤት ሙግት ይጀመራል። ሁለቱም ወገኖች ዋስ ከጠሩ በኋላ ዳኛው ተከሳሹ ክሱን እንዲያቀርብ ይጠይቀዋል። ተከሳሹ ይገባኛል የሚለውን ሁሉ ጠይቆ እንደጨረሰ፥ ተከሳሹ የእምነት ወይም የክህደት ቃሉን እንዲሰጥ ይጠየቃል።

ክሱን የካደ እንደሆነ የከሳሹ ጠበቃ ዘንጉን እየተመረከዘ በችሎቱ ከዳኛ ፊት ወደፊት ወደኋላ እየተንጎራደደና እየተንደረደረ በአከራካሪው ጉዳይ ያለውን የፍሬ ነገርና የጥፍጫሬ ክርክሩን ያቀርባል።

ተከሳሹ ደግሞ በፋንታው ፍጆታ ጠይቆ፥ በዚሁ አኳኋን መከራከሪያውን /ተቃውሞውን/ ያቀርባል።

### ለ/ ውርርድ መትከል

በዚህ ደረጃ ከሳሽ ጭብጡን ለማሳመን ውርርድ ይተክላል። ተከሳሹ ሲፈልግ፤ ለምሳሌ ከሳሽ በቅሎ እሰጥ ብሎ ውርርድ ተክሎ እንደሆነ፥ ውርርድህን እሰልስል /ዝቅ አድርግ/ ብሎ ይጠይቃል። ከሳሽ ፈረስ እሰጥ በማለት ውርርዱን ዝቅ ካደረገለትም በኋላ እንደገና ዝቅ እንዲያደርግለት ከፈለገ እንደገና እሰልስል ብሎ ሊጠይቅ ወደ ማር[9] ያወርድለታል። ተከሳሹ ከዚህ በኋላ ለከሳሹ የተከለውን ማር የሚሰጥ ለመሆን "እገና" ብሎ ይከራከራል። አለበለዚያም "እምና ይጓገቷል፥

ከረከሰበት ይሸምቷል" እንደሚባል፣ ጉዳዩን እምና ተፋተኛ የማይሆንበትን ምክንያት ውርርድ ተከሉ ያስረዳል። ተከሳሹ የቀረበበትን ክስ እርግጠኛነት ያመነ እንደሆነ ግን ለተተከለበት ውርርድ "አትራሀ ጠናኝ" ይባላል።

እንደዚህ ያለው የእምነት ቃል ሲሰጥ ከሳሹ "በአትራሀ ጠናኝ የተረታ፥ መሐል አገዳውን የተመታ" ብሎ ቀኙ የእርሱ መሆኑን በቃለ አጋና በመግለጽ፣ በተከሳሹ ላይ እንዲፈረድበት ይጠይቃል። አትራሀ ጠናኝ ያለው ወገን አንድ ብር የዳኝነት እንዲከፍል ይጠየቃል።

በአትራሀ ጠናኝ የተፈጸመ ክርክር ይግባኝ የሌለው፥ የነገር መደምደሚያ ነበር።

ሐ/ <u>የምስክሮች አመሰካከርና የጽሁፍ ማስረጃ አቀራረብ</u>

ተከሳሹ ከቀረበበት ክስ እንዳንዱን ሁኔታ የሚክድ የሆነ እንደሆነ፣ የተካደው ጉዳይ በአስረጂ መረጋገጥ አለበት፣ ስለዚህ ከሳሹ ክሱን ለማስረገጥ በቃል ወይም በጽሁፍ ወይም በሁለቱም አስረጂውን ያቀርባል።

ሁለቱም ወገኖች ውርርድ ከተከሉና በመካከላቸው አከራካሪው ጭብጥ ተለይቶ ከታወቀ በኋላ በያንዳንዶቹ ወገን የሚቀርቡ፥ ቢያንስ ሦስት ሦስት ምስክሮች ይሰማሉ። ምስክሮቹም ከፍርድ ቤት ቀርበው ሁለቱም ወገኖች ወይም ነገረ ፈጆቻቸው በአሉበት በግልጽ ይመሰክራሉ። የጽሁፍ ማስረጃ ካለም ለፍርድ ቤቱ ይቀርባል። እዚህ ላይ በጭብጥ ዳኛ[10] አማካይነት የተገኘ መረጃ ተቀባይነት ያለው መሆኑንና የበቂነት ዋጋውን መረዳት ተገቢ ይሆናል።

በእርጅና ወይም በብርቱ ሕመም ምክንያት አንድ ምስክር ከፍርድ ቤት ቀርቦ ለመመስከር ያልቻለ እንደሆነ፣ ለማመሳከር በተሰየመ የጭብጥ ዳኛ አማካይነት የተባለው ምስክር ቃል ተሰምቶ ለፍርድ ቤቱ እንዲፈለስ ይደረጋል። የጭብጥ ዳኛው በክርክሩ ጊዜ የተነሳው ጭብጥ ይገለጽለትና ምስክሩን አስመስክር ለፍርድ ቤቱ

እንዲያፈስ ይጠየቃል። አስመስካሪው ከተከራካሪዎቹ ጋር ምስክሩ ወደ ሚገኝበት ሥፍራ ይሄዳል። ተከራካሪዎቹ ወገኖችና የአካባቢው ጭቃ ሹም የመረጡአቸው አራት እማኞች በተገኙበት ምስክሩ የሚሰጠውን አድምጦ ሲመለስም፣ ተከራካሪዎቹ በተገኙበት ለላከው ዳኛ ምስክሩ የመሰከረውን በቃል ያፈሳል /ይገልጻል/።[11]

የጭብጥ ዳኛው የምስክሩን ቃል ሲያፈስ ያዳነፈ /ያሳሳተ/ እንደሆነ የሚታረምበት ሁኔታ እንደሚከተለው ነበር።

> ምስክሩ ከተናገረው ቃል ውስጥ ያስቀረ ወይም የጨመረ እንደሆነ ቅር የተሰኘው ወገን "ተዘከረኝ ዳኛ ማርያም፤ እግዚአብሄር መዝከሪያ ልቡና መተላለፊያ ጎዳና ይስጥህ፤ እቶ እገሌ እንዲህ የመሰከረ መሆኑን አስታውስ ይለዋል።"[12] የተዘነጋው ነገር ቢኖር ያቃናል። በቃሉ የፀና እንደሆነ ግን፣ ተቃዋሚው "የምስክሩን ቃል በማጣረሱ ሰድቤሃለሁና ምስክሩን የሰሙት እማኞች ይንቀሉልኝ" ይላል። በዚህ ጊዜ እማኞቹ እንዴት እንደተመሰከረ ይጠየቃሉ። እንደርሱ ነው ብለው የመሰከሩ እንደሆነ ነቃፊው አመስካሪውን ዳኛ ይከሳል። እንድሉ የተገኘ እንደሆነ ግን የምስክሩ ድምፅ እማኞቹ እንደተናገሩት ሁና ይፀናል። ዳኛውም ይወቀሳል።

በመሠረቱ በጥንቱ ልማድ ምስክር የምስክርነት ቃሉን ከመስጠቱ በፊት ቃለ መሐላ እንዲሰጥ አይጠየቅም። ሆኖም "አምልሃለሁና የምታውቀውን አስተካክለህ መስክር" ብሎ ማስጠንቀቅ ይቻላል። የማስጠንቀቂያቸውም ቃል "ስማ ምስክር እንዳትል" የሚል ነበር።

ከሳሽ ወይም ተከሳሽ ምስክሩ የሚያውቀውን በትክክል አለመመስከሩን ወይም መሸፈጡን ሲረዳ ለማስማል እንዲፈቀድለት ዳኛውን ጠይቆ፣ ወደ ቤተ ክርስቲያን

ጃደው በቅዳሴ ጊዜ ዕርገት ሲወርዱ የቤተ ክርስቲያኑን በር ይዘጋል[13] ወይም መጽሐፍ ቅዱስ ይዞ እውነቱን ባለመስከር

እንደ መስቀሉ ይበሳሳኛ
እንደ ሥዕሉ ይደምስሰኛ
እንደ ሥጋው ይቆራርሰኛ
እንደ ደሙ ያፍሰኛ
እንደ መቅደሱ በር ልሳኔን ይዝጋው

እያለ ይምላል።

አንድ ምስክር ከፍርድ ቤት ከመቅረቡ በፊት ሲመሰክር /የምስክርነት ቃሉን ሲሰጥ/ የተገኘ እንደሆነ፣ ሌላው ወገን አስቀድሞ የመሰከረ ስለሆነ አይነገርብኝም ወይም ለምስክርነት አይበቃም ብሎ የመቃወም መብት አለው።

አንድ ምስክር ሲቆጠር፣ ሌላው ወገን "እገሌ ለባላጋራየ የሥራ ወይም የጋብቻ ዝምድና አለው፣ ወይም አበልጅ ወይም የጉድፈቻ ልጅ ነው" በማለት ወይም ነውር በመጥቀስ እንዳይመሰክር ብይ /እክይ/ ሊያወጣበት ይቻላል።[14] ምስክሩም የምስክርነት ቃሉን ከመስጠቱ በፊት የቆጠረው ወገን፣[15]

ሞቶ መኮነን
ታሞ መመንመን
የአልጋ ቁራኛ መሆን

ያለ መሆኑን ተገንዝበሀ፥ እውነቱ እንዲህ መሆኑን ብታውቅልኝ ይለዋል።

ሌላውም ወገን በዚሁ አኳኋን ካዘከረ በኋላ፣ "እንደተባለው ለመሆኑ ባታውቅብኝ" ብሎ ይናገራል።

የምስክሮች ሁሉ ቃል ከተሰማ በኋላ አብዛኛዎቹ ምስክሮች የመሰከሩለት ወገን "ምስክር ለበለጠ፣ ውድማ ለመለጠ" በማለት፤ መብቱ ስለተረጋገጠለት ፍርድ እንዲሰጠው ይጠይቃል።

ምስክር ሲመሰክር ለኔ ነገረ፣ ለኔ ነገረ በማለት ሁለቱ ወገኖች የሚሻሙበት ሁኔታ ያጋጥማል። እንደዚህ ያለ ሁኔታ ሲያጋጥም፤ እርጥብ እማኞች[16] ተመርጠው "ምስክሮቹ የነገሩት ለተከሳሹ ወይም ለከሳሹ ነው" ብለው በመሰላቸው ያደሉ ነበር። በኋላ ግን ምስክሩ ራሱ ለማን እንደመሰከረ እንዲያረጋግጥ እንደገና እንዲጠራ ይደረግና በሚሰጠው ቃል[17] በዚህ ረገድ የተነሳው ክርክር ፍጻሜ እንዲያገኝ ይደረግ ነበር።

መ/ ተጠየቅ

በቀድሞ ጊዜ በፍትሐብሄር ክርክር የመከላከያ ምስክር በማቅረብ የመከላከል መብት አልነበረም። ተከሳሽ ክስ ለቀረበበት ነገር "ማስረዳት የሚገባኝ እኔ ነኝ እንጂ ከሳሽ አይደለም" ብሎ በይገባል ይከራከር ነበር።[18]

ራሽረገድ ራሴል ስለዚህ ዓይነቱ የክርክር ዘዴ ሲያትቱ፤ ከአንድ ተኩል ምዕተ ዓመታት በፊት እንደሚከተለው ጽፈዋል።

> ጠበቆቹ እንደነገሩ ሁኔታ ከከሳሹ ወይም ከተከሳሹ ጎን ይቆሙና ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ልዩ ልዩ ክርክሮቻቸውን ያቀርባሉ። በዚሁም ሂደት በክሱ ውስጥ የተመለከተውን እንደዚህ እንደዚህ ያሉትን ክርክሮች ለማስረገጥ በቅሎ፣ ላም፣ በግና ወርቅ እሰጥ በማለት ተናጋሪዎቹ እያደራረሱ ውርርድ ይተካላሉ።[19]

እንደዚህ ያለው በሥነ ሥርዓት የመጠቀም መብት በተከራካሪዎቹ ወይም በነገረ ፈጆቻቸው ይነሳ ነበር። እንደዚህ ያለው ክርክር ሲነሳበት ሌላው ወገን ካፈ[20] ወይም ከጠበቃየ[21] ይላል።

በተወሰነው ቀነ ቀጠሮ በተጠየቀ የሙግት ሥርዓት መሠረት በጥያቄና መልስ ክርክሩን ለመፍታት ክርክሩን ከመጀመሩ በፊት ከሳሽ ራሱ ወይም በነገረ ፈጅ አማካይነት "ሥርዓት ልክ ነው?" ብሎ ይጠይቀዋል። ተከሳሹ አወንታዊ መልስ ስለሚሰጥ፤ ክሱ የሚያስከትለውን ሁኔታ ለማስገንዘብ፥ ከሳሹ ልዩ ልዩ ጥያቄዎችን ያቀርባል።

ጠያቂው በአንድ ጊዜ እንዲያቀርብ የሚፈቀድለት አንድ ጥያቄ ሲሆን፥ ተከራካሪውም ወገን ለያንዳንዱ ጥያቄ አንድና ቀጥተኛ የሆነ መልስ መስጠት አለበት። በዚህ አኳኋን በተከራካሪዎች ወገኖች መካከል የጥያቄና መልስ ልውውጥ ይደረጋል። ለዚህም ሥርዓት መከበር ውርርድ ይተከላል። ከተጠየቀው ውጭ ወይም ተረፍረፍ አድርጎ የመለሰ እንደሆነ ሥነ ሥርዓቱን እንደማጣረስ ይቆጠራል።[22]

ከተከራካሪዎቹ ወገኖች አንደኛው ይህን ሥነ ሥርዓት ያጣረሰ እንደሆነ አስቀድሞ የተሰነዘረውን ውርርድ ለመክፈል ዋስ እንዲጠራ ይጠየቃል። ለቀረበው ጥያቄ በተሰጠው መልስ ሥነ ሥርዓት መጣረስ ወይም አለመጣረሱ በተችዎች ይረጋገጣል። እንደዚህ ያለ ስህተት ማድረጉን ተጠያቂው ቢያምንም እንኳ ውርርዱን መክፈል አለበት። ከሣሽ ጥያቄዎቹን ሲጨርስ፥ ተከሳሹ በፋንታው ጥያቄዎች ማቅረብ ይቀጥላል።

ሠ/ <u>ውርርድ መንዛት ወይም በላ ልበልሃ</u>

በክሱ ላይ ዋና ጥያቄና መስቀለኛ ጥያቄ የማቅረብ ጉዳይ እንዳበቃ፥ ዳኛው ውሳኔውን ከመስጠቱ በፊት ተከራካሪዎቹ ውርርድ ወደ መንዛት ያመራሉ። ማለትም በግጥምና በርቱዕ አንጋገር ዳኛውንና በፍርድ ቤቱ የተገኙትን ሰዎች ለማሳመን የበላ ልበልሃ ሙግቱን ያሹጎደቱዱታል።

በዚሁም ጊዜ እያንዳንዱ ወገን የበላጋራውን ነውሩን፣ በዘሩ ጭምር ያለበትን መዘርዘር፣ በጀርኔ እያሰደበ የተቀማውን ሐሳብ ወደርሱ ለመሳብ፣ ነገሩን በሚመስል ሁኔታ እያብራራ በግጥም እያደረገ፣ ምሳሌ እየሰጠ ውርድ ይንዛል ወይም የመፋረጃ ቃሉን ይሰጣል።

የሚከተለው የውርድ አነዛዙን በመጠኑ ያመለክታል:-
በላ ልበልሃ፣
የአጤ ሥርዓቱን[23] የአብርሃም እረቱን፣ የመሠረቱን
አልናገር ሐሰቱን፣ ሁልጊዜ እውነት፣ እውነቱን፤
ከ ... ወዲያ ላኛ
ከ ... ወዲያ ዝንገኛ
አልተፈጠረም ላገመኛ
... የፈረደው
የአዳል ዱቤት ያረደው፣
የፈረደው አይገለበጥ
ያረደው አይንፈራገጥ።
እሰጥ ብየ ማር ጥየ
ከእገር ዘንጥየ
ባለማ ፍረዱልኝ፣
ባጠፋ ስደዱኝ፤
ሲል ይሟገታል፤ እፌ ማሩ ነገረ ደግሞ።[24]

ሌላውም ወገን በተራው በዚሁ ዓይነት ላኛውን ለመሳብና ተከራካሪውን ለማዋረድ ይጥራል።

የሚለዋወጡዋቸው በስሜት የተሞሉ ቃላት ቢሆኑም፤ በጥያቄው ጊዜ ያስተማመነውንና ከቃሉ ያገኘውን መልስ ለክርክሩ እንዲደግፈው ባላጋራው

የሚያብራራበትና የራሱን ቀጥተኛነትና እውነተኛነት የሚገልፁባቸው ሲሆኑ፣ በዘመናዊ ሙግት ለውሳኔ በደረሰ ነገር ዳኛው ከመፍረዱ በፊት እንደሚቀርበው የመፋረጃ ቃል ያለ ነገር ነው።

የውርድ መንዛት ሌላው ዓላማ የዳኛውን ልቦና ማሞካሸት ነው። በዚህ ረገድ ባሻ ሙላት ወልደ ዮሐንስ የተባሉት ነገር አዋቂ፣ በአፈንጉሥ ነሲቡ ችሎት ላይ የተናገሩት የሚከተለው ግጥም የአፈ ንጉሥ ነሲቡን ልቦና ሰቅሎት እንደነበረ ይነገራል። ግጥሙም:-

እሳት ላይ የጣሉት ነት
አልጋ ላይ ያነጠፉት ቁርበት
ለእሰተኛው እንደነቱ
ለእውነተኛው እንደቁርበቱ
ነው ነሲቡ ዳኝነቱ።
ፈረሱ ዳማ፣ ሚስቱ ደስታ
ጎራዴው ወንበዴ ዞር የሚመታ
ጌታዬ አንተ ፊት አሰት ይዤ አልመጣ
ቀጣፊ ወንበዴ ለይተህ በጅራፍ እምትቀጣ።[25]

የሚል ነበር።

ክርክሩ የውርድ መንዛቱን ደረጃ ሲያልፍ፣ ተቾዎች /እማኞች/ ከታች በመጀመር ወደ ላይ በየተራ እየተነሱ የመሰላቸውን እየተቹ እንዲፈርዱ ይጠየቃሉ።

ረ/ <u>መተቸትና ፍርድ መስጠት</u>

በፍርድ ጊዜ እማኞችም ሆኑ ወይም ዳኛው ለመፍረድ ሲነሱ የሚከተለውን ቃለ መሐላ ያደርጉ ነበር።

ይፍረድብኝ፥ ይፈረድብኝ
ባደላም ያድላብኝ
በጌታየ ጠላት ሠይፍ፥ ሞት ይፈረድበት፤
የራቀን በመድፍ የቀረበውን በሰይፍ
አርዶ፥ ፈርዶ ይጣለው።[26]

ተችዎቹ /አማፆች/ ፍሬ ነገሩን ካብራሩ በኋላ "እነሌ ሲረታ ይታየናል" በማለት አስተያየታቸውን ይገልጻሉ።

በመጨረሻም ዳኛው /ወንበሩ/ በቅድሚያ ምክንያቱን ከተነተነ በኋላ "እነሌ ፈርጄብሃለሁና ውርርድህን አንሳ"[27] በማለት እንደነገሩ ሁኔታ፥ በተከሳሹ ወይም

በከሳሹ ላይ ፍርዱን ይሰጣል።

ፍርድ ቀጠነብኝ ባይ ይግባኝ ካላለ በቀር ክርክሩ በዚሁ ያበቃል።[28]

ሰ/ <u>ይግባኝ ማስማት</u>

ይግባኝ በፍሬ ነገር ወይም በይገባል ወይም በተፍጻሜ ሊመሠረት ይቻላል። በማንኛውም ፍርድ ወይም ጊዜያዊ ትዕዛዝ የሚቀርብ ቅሬታ በዳኞች ብቻ ሳይሆን በቆርቋሪዎች ማለትም በፍርድ ቤቱ በተገኙ ተችዎች ጭምር ይመረመራል።

በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ በቁጥር 184 እንደተመለከተው የትእዛዝ ይግባኝ እምብዛም አልነበረም። በተፍጻሜ ጉዳይ የተሰጠው ትእዛዝ የፍሬ ነገሩን ክርክር የሚጎዳበት መስሎ ሲታየው፤ ከተከራካሪዎቹ አንደኛው ወገን በፍርድ ቤቱ በተሰጠ ትእዛዝ ይግባኝ ለማለት ይችል ነበር። ለምሳሌ በባለንብረትነት ክርክር በአንድ በተለየ ኅብረተሰብ ልማዳዊ ሕግ የቅድሚያ መብት /ፕሪኤሚቲቭ ራይት/

ስለመኖሩ፥ በማስረዳቱ ዘዴ ረገድ በተፈጻሚው ክርክር ላይ ብያኔ መስጠቱ ወዲያውኑ መፍትሄ ካልተገኘ በቀር የተከራካሪውን ጥቅም የሚጎዳ ሆኖ ሲገኝ፤ በተፈጻሚ ጉዳይ በተሰጠ ትእዛዝ ይግባኝ ማቅረብ፥ በቂ ምክንያት ሁኖ ይቆጠር ነበር።

ለበላይ ፍርድ ቤት በተለይም ለአፈ ንጉሡ[29] የሚቀርበው ሌላው ነገር የሕግ አተረጓጎም ጥያቄ ነበር። የይግባኝ ክርክር፤ ማለትም አንድን ክስ የማስረዳት መብት ያለኝ እኔ ነኝ የሚለው ክርክር እና የሕግ ትርጓሜ ጥያቄ የሚቀርበው በራስ ወንበሮች[30] ለሚታገዘው ለአፈ ንጉሡ ነበር። አንድ ዓይነት ሁኔታ እንዴት እንዲፈታ ወይም ጥያቄዎች እንዴት እንደሚተረጎሙ አመራር ለማግኘት፥ የበታች ፍርድ ቤት ዳኞች ጉዳዩን የሚያስተላልፉት ለዚህ ፍርድ ቤት ነበር።

## 3. ማጠቃለያ

ባለፈው ምዕተ ዓመትና በያዝነው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ላይ በተጠየቅ ሙግት ሥርዓት ይካሄድ የነበረው የክርክር ሥልት ፍጹም ኢትዮጵያዊና ልዩም ነበር።

ከዚህ በላይ በአጭሩ እንደተገለጸው የጥንቱን የኢትዮጵያ ሕግ ጠለቅ ብሎ ለመረመረ ከመሠረታዊ ሕጎች ይልቅ የሥነ ሥርዓት ሕጎች በይበልጥ መዳበራቸውን መረዳት ይቻላል። ይህም ሊሆን የቻለው የፍትሐ ነገሥት[31] ሊቃውንት በሚያስተምሩት፤ በአገረ ገዢዎች፥ በቤተ መንግሥት ችሎቶች ላይ በመዋል ወጣቶች የፍርድ ሥርዓት እንዲለማመዱ በማድረግ ለፍትሕ በሚሰጠው ከፍተኛ ልማዳዊ ግምት ምክንያት ሁኖ ይገኛል። ሙግት ቢያንስ የመንገድ ዳር ፍርድ ቤትን በተመለከተ በበጎ ፍቃድና ወዲያውኑ የሚከናወን መሆኑ፤ የፍትሕ አስተዳደር ለማንኛውም ሕግ አክባሪ ዜጋ ሕዝባዊ ጉዳይ እንዲሆን ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል። ይህንና ሌሎች ሁኔታዎች ተጣምረው፥ ልማዳዊ የሥነ ሥርዓት ሕግ በአንጻራዊ አገላለጽ በይበልጥ እንዲዳብር ለማድረግ አስችለዋል።

## ማስታወሻዎች

1. እሰጥ አገባ ማለት ውርርድ መትከል፤ ማለትም ባላጋራው እሰጣለሁ ያለውን ውርርድ ቢረታ ለመክፈል መስማማት ማለት ነው። ጂበጂ ለማ የጥንቱ እሰጥ አገባ ሙግት፥ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ክፍል የቀረበ የመመረቂያ የምርምር ጽሁፍ /ያልታተመ፤ ከሕግ ፋኩልቲ አርሽብ፤ 1965 ዓ.ም./

2. ቨርጂን ኤሪክ ዘ አብሲኒያ አይ ኒው (ሎንደን፥ ማክሚላን ኤንድ ካምፓኒ ሊሚትድ እ.ኤ.አ 1936) ገጽ 91፥ በጂበጂ ለማ የጥንቱ እሰጥ አገባ ሙግት ገጽ 2 የተጠቀሰ።

3. በብዙዎቹ የታወጁ ሕጎች መቅድም ላይ ማንኛውም ሰው በተላላፊ መንገደኛ ላይ ባላጋራውን ለመክሰስ መብት እንዳለውና ተላላፊ መንገደኛው እንደዳኛ ሆኖ ለማገልገልና ፍትሕ ለማስገኘት ሥልጣን እንዳለው ይገልጽ ነበር።

4. የመንገድ ዳር ዳኛ የተጠየቅ ሙግትን ሥርዓት አይከተልም።

5. ጭቃ ሹም የሚባለው የአንድ የተወሰነ አካበቢ ሹም ነው።

6. መልከኛ የቀበሌ ገዥ ነው።

7. በተለያየ ደረጃ በሚገኙ ፍርድ ቤቶች ቁጥራቸው የተለያዩ ተቺዎች ወይም ቆርቋሪዎች በሁለት ተከራካሪ ወገኖችና በዳኛው ይመረጡ ነበር። ቁጥራቸውም ከስድስት እስከ ስምንት ይለያይ ነበር።

8. በሁሉም ክሶች ሁሉም ዓይነት ዋሶች አይጠሩም።

9. ይህም በገንዘብ ይከፈል የነበረ ውርርድ ነበር። ማለትም በማር ለተተከለ ለያንዳንዱ ውርርድ አራት ብር ይከፈል ነበር።

10. ለማመሳከር የሚመደብ ዳኛ ነው።

11. ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል የኛም እሉ እንውታቸው /አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት 1958 ዓ.ም. ያልታተመ/ ገጽ 8።

12. ዝኒ ከማሁ።

13. የቤተ ክርስቲያን በር የሚዘጋው ለከፍተኛ ጉዳይ ብቻ ነው።

14. የቀድሞ ዳኛና ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣን ከሆኑ፣ የጥንቱን የሙግት ሥርዓት ከሚያውቁ ከፊታውራሪ አበበ ገብሬ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ።

15. ዝኒ ከማሁ።

16. የተለየ ጭብጥ ለመስማት የተመረጡ ተችዎች።

17. ማኅተመ ሥላሴ ከዚህ በላይ በተጠቀሰው በገጽ 40።

18. ዝኒ ከማሁ።

19. ጂበጂ ለማ ከዚህ በላይ በተጠቀሰው በገጽ 2።

20. "ከእፊ" ማለት ተነጋጋሪየን ይዤ መቅረቢያ ጊዜ ይስጠኝ በማለት የሚቀርብ ጥያቄ ሲሆን፤ እንደዚህ ያለው ጥያቄ የሶስት ቀን ቀጠሮ ያሰጣል።

21. "ከጠበቃዩ" ማለት ጠበቃ ይዞ የመቅረቢያ ጊዜ እንዲሰጥ የሚቀርብ ጥያቄ ሲሆን፤ የሰባት ቀን ቀጠሮ ያሰጣል።

22. ማኅተመ ሥላሴ ከዚህ በላይ በተጠቀሰው ገጽ 40።

23. ቀጥታ ትርጉሙ የንጉሥ ማለት ሲሆን፥ በፍርድ ቤት በመሠረታዊ ሕግነት ወይም በሥነ ሥርዓት ሕግነት በአገሪቱ ተቀባይነትና ተፈጻሚነት ያለውን የልማዳዊ ሕግ መርሆዎች መጥቀስ ማለት ነው።

24. ማኅተመ ሥላሴ ከዚህ በላይ በተጠቀሰው በገጽ 40-41።

25. ከቀድሞ የመንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣን ከቢትወደድ ዘውዴ ገብረ ሕይወት ጋር የተደረገ ቃለ መጠየቅ።

26. ማኅተመ ሥላሴ ከዚህ በላይ ከተጠቀሰው ገጽ 39።

27. ከፊታውራሪ አበበ ገብሬ ጋር ከተደረገ ቃለ መጠይቅ።

28. ከ1928 ዓ.ም. በፊት የነበረው የመደበኛ ፍርድ ቤቶች የተዋረድ ደረጃ የሚከተለው ነበር:-

    1. የዙፋን ችሎት
    2. የአፈንጉሥ ፍርድ ቤት /ብሄራዊ ሥልጣን ያለው/
    3. የሻለቃ ፍርድ ቤት /አውራጃ ፍርድ ቤት/
    4. የአካል ዳኛ /የወረዳ ፍርድ ቤት/
    5. የሥር ወይም የአፈር ዳኛ /የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት/

29. "አፈንጉሥ" የሚባለው የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ፕሬዚዳንት ነበር።

30. "ራስ ወንበሮች" የሚባሉት አፈንጉሱን እንዲያግዙ በማዕከላዊ መንግሥት የሚሾሙ ሹሞች ሲሆኑ፣ በስድስት ችሎት ተከፍለው ከተመደቡባቸው ክልል የሚቀርቡ ይግባኞችን የሚሰሙ ሹሞች ነበሩ።

31. ፍትሐ ነገሥት በ15ኛውና በ16ኛው ምዕተ ዓመት መካከል ወደ ኢትዮጵያ የገባና በዳግማዊ አጼ ምኒልክ በ1900 ዓ.ም. ከኢትዮጵያ ሕግ ተርጓ የገባ የሕግ መጽሀፍ ነው።